# <u>የኒውክለር መዘዝ</u>

**<u>(ዮሀንስ አልታሞ)</u>**




ሰባ ሁለት አመታት ተቆጠሩ ። የጃፓን ሁለቱ ከተሞች ሂሮሽማ እና ናጋሳኪ በአሜሪካኖቹ ቢ-29 የኒውክለር ቦምብ ጣይ የቦይንግ ስሪት ጀቶች  አስራ ስድስት ኪሎ ቶን እና ሀያ ኪሎቶን የፍንዳታ አቅም  ያላቸው የኒውክለር ቦምቦችን በሁለቱ ከተሞች በሶስት ቀናት ልዩነት አፈራርቆ  በማፈንዳት አራት መቶ ሀምሳ ሺ የሚገመት ህዝብን ከፈጁ ወዲህ ያለፉ አመታት ።

ባሳለፍነው ሳምንት የጃፓን መንግስት እና ህዝብ በእነኝያ ሰቅጣጭ ቀናት የተፈጸሙ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች በሰው ልጆች ታሪክ ዳግም እንዳይከሰቱ መልዕክት በሚያስተላልፍ መልኩ ሰባ ሁለተኛ አመት መታሰቢያ ቀን አክብረዋል።

በሂሮሽማ ከተማ የተጣለው “ትንሹ ልጅ “እና የናጋሳኪው “ወፍራሙ ሰውየ” የተባለ ስያሜ የተሰጣቸው ሁለቱ  የአቶሚክ ቦምቦች ጃፓን ለሁለተኛው የአለም ጦርነት አሸናፊዎች እጇን እንድትሰጥ ያስገደዷት ሲሆን የኒውክለር ቦምብ ጥቃትን በአገሯ ያስተናገደች የመጀመሪያዋ አገር አድርጎታል። እስከ አሁን ባለው ሁኔታም የመጨረሻዋ ሆናለች። ከዚያ ወዲህ አገሪቱ ከኒውክለር የጸዳ አለም እንዲፈጠር ቀዳሚውን ሚና በመጫወት ትታወቃለች። ከዚሁ ጋር የተገናኙ  አለም አቀፍ የቃልኪዳን ስምምነቶችን በአብዛኛው ሊባል በሚችል ደረጃ ፈርማለች ። በመሆኑም እስካሁን የኒውክለር የጦር መሳሪያ አታመርትም። ሆኖም ለሀይል ምንጭነት የኒውክለር ሀይልን ታመርታለች።

ለጃፓናውያን የኒውክለር የጦር መሳሪያ ማምረት  የሂባኩሻዎችን መብት እንደመርገጥ ይቆጠራል። ሂባኩሻ- ጃፓንኛ ቃል ነው። የቃሉ ቀጥተኛ ትርጎሜ በሁለቱ የጃፓን ከተሞች በተጣሉ የኒውክለር ቦምቦች ፍንዳታ ምክኒያት ጥቃት የደረሰባቸው ነገር ግን በህይወት የተረፉ ጃፓናውያንን ለመግለጽ ከጥቃቱ ወዲህ በጃፓናውያን የተፈጠረ ቃል ነው። ሂባኩሻዎች ለኒውክለር ጨረር በመጋለጣቸው

ምክኒያት ከደረሰባቸው ጉዳት ጋር በተገናኝ በሌላው ህብረተሰብ የመገለል አዝማሚያ የሚያስጨንቃቸው ከመሆኑም ባሻገር መንግስት ነጻ እና ዘላቂ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ለበርካታ አመታት እንደ አንድ የተለየ የህብረተሰብ ክፍል በመሆን ከፍተኛ ትግል አድርገዋል። በዚህም ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል በተለየ መልኩ የተለያዩ መብቶቻቸው የጤና አገልግሎትን ጨምሮ ተከብሮላቸው በነጻ እንዲያገኙ ተደርገው ይኖራሉ ። ሂባኩሻዎች የኒውክለር ምርት በጃፓንም ሆነ በየትኛውም የአለም ክፍል እንዳይመረት ከፍተኛ ቅስቀሳ ለማድረግ ራሳቸውን የሰጡ አክቲቪስቶችም ናቸው። ለዚህም ጥቃቱ ከተፈጸመ ከሰባት አስርት አመታት በኃላም ቢሆን በተለያዩ የጤና እክሎች ላይ ቢቆዩም በየአመቱ ከሁሉም ስፍራ በመሰባሰብ ለአለም ማህበረሰብ ከኒውክለር የጸዳች አለም እንድትፈጠር መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ ። ባሳለፍነው ሳምንትም በጃፓን ምድር የተከበረው የመታሰቢያ በአል ከዚሁ ጋር የተገናኘ ነው ።

በአለማችን አወዛጋቢ እና አደገኛ ከሚባሉ የፓለቲካ ክስተቶች አንዱ የኒውክለር የጦር መሳሪያ ምርት ጉዳይ ነው። የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ላይ የተወሰኑ አገራት የመሳሪያው ባለቤት ነበሩ ። እንደ አሜሪካ እና የሲቪየት ህብረት ። እነዚህ ሁለቱ ያላቸውን ሀይል በፍጥነት ከማጠናከር ይልቅ ቅነሳ እያሳዩ መጥተዋል። የዘርፉ ባለሙያዎች "ቨርቲካል ፕሮሊፍሬሽን" ይሉታል ይህ እየቀነሰ እንደመጣ ይናገራሉ ። ከምርት ጋር በተገናኘ ትልቁ አሳሳቢው ጉዳይ ከዚህ ቀደም ኒውክለር ያልነበራቸው አገራት ለመታጠቅ የሚያደርጉት ጥድፊያ እና ተነሳሽነት ዋነኛው ችግር መሆኑ ነው። ይህንን "የሆሪዘንታል ፕሮሊፍሬሽን" ብለውታል እየጨመረ መሆኑን በመግለጽ።

ህንድ እና ፓኪስታን ታጥቀዋል መሳሪያውን ታጥቀዋል ። እስራኤልም ትታማለች ከዚያም ባለፈ የኒውክለር ምርት ለመግታት የተዘጋጀውን ስምምነት "ኒውክለር ነን ፕሮሊፍሬሽን" ስምምነት አልፈረመችም ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሰሜን ኮሪያ እና ኢራንም እንዳላቸው እየተደመጠ ነው፣ ጥቂቶች ደግሞ የነበራቸውን ወደ ማውደም ደረጃም የተሸጋገሩ አሉ። ለአብነት ደቡብ አፍሪካ እ.ኤ.አ በ1991 በራሷ ፍቃድ ስድስት ያለቀላቸው የኒውክለር ቦምቦችን አውድማለች ። ዩክሬን እና ቤላሩስ እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ የሶቬየት ህብረት መፈረካከስ ተከትሎ ቀደም ሲል ወርሰው የነበሩትን ለሩሲያ መልሰዋል። እነዚህ እርምጃዎች በተጠቀሱ አገራት የተወሰዱት በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የጦር መሳሪያ ቁጥጥር ከማድረግ ጥረት ጋር ተያይዞ የወሰዱት እርምጃ እንደሆነ ይነገራል።

የኒውክለር መሳሪያ ስርጭት ጉዳይን አስመልክተው የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ እ.ኤ.አ እ.ኤ.አ በ1963 እንደተናገሩት ቁጥጥር ካልተደረገ ከሀያ የማያንሱ አገራት የንውክለር መሳሪያ በአስር

አመት ጊዜ ውስጥ ወደ ታጠቁት አገራት ጐራ/ካምፕ/ መቀላቀላቸው እንደማይቀር ትንበያቸውን አሳውቀው ነበር ። የተናገሩት አልቀረም። በአጭር አመታት ጊዜ ውስጥ የኒውክለር ማብላያ ወደ መትከል የተሸጋገሩ አገራት ቁጥር ጨመረ ። በዚህም ኒውክለር ያልታተቁ አገራ እንዳይታጠቁ ክልከላ የሚያደርገው ስምምነት ትርጉም እየሆነ መጣ። የስምምነቱ ዋና መነሻ ሀሳብ የነበረው ስርጭቱ ገደብ ካተበጀለት ብዙ አገራት የኒውክለር ባለቤት ከሆኑ መሳሪው ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልበት እድል የዚያኑ ያህል ይጨምራል የሚል ነበር። እ.ኤ.አ በ1968 የተፈረመው ይሄው የእገዳ ስምምነት መርሆዎቹ ይሄንኑ ዋነኛ ግብ ማሳካትን ታሳቢ ያደረገ ነበር ።

የእገዳ ስምምነት መርሆች ከሆኑት መካከል የኒውክለር የጦር መሳሪያ ባለቤት የሆኑ አገራት ወደ ሌሎች ኒውክለር አልባ አገራት የኒውክለር ቴከኖሎጂ እንዳያሸጋግሩ፣ኒውክለር የሌላቸው አገራት የኒውክለር የጦር መሳሪያ እንዳያለሙ፣ሁሉም የኒውክለር መሳሪያ የሌላቸው ነገር ግን ኒውክለርን ለሀይል ምንጭነት ለመጠቀም የሚያስቡ እና የሚያለሙ ከሆነ ከአለምአቀፍ አቶሚክ የሀይል አጀንሲ ጋር ኤጀንሲው በየወቅቱ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችለውን ስምምነት እዲያደርጉ እንዲሁም ቀደም ሲል የኒውክለር ጦር መሳሪያ የታጠቁ አገራት ተጨማሪ ምርት ላለማምረት እና ያላቸውንም ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት ድርድር ውስጥ እንዲገቡ የሚሉ ናቸው።

በዚሁ መሰረት በአለማችን በኒውክለር አጀንዳ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ምክክሮች ፣ ድርድሮች እና ስምምነቶች ከላይ የተመለከቱ አራት መሰረታዊ መርሆችን መነሻ እና መድረሻ ያደረጉ ናቸው።

በእርግጥ የኒውክለር ስርጭር እገዳ ስምምነት ድርድር በተካሄደበት ወቅት አሜሪካ፣ ሩሲያ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና ቻይና የኒውክለር የጦር መሳሪያ ቀደም ሲል የታጠቁ መሆናቸው እውቅና ያለው መሆኑ ፣መሳሪያውን ሙሉ በሙሉ ለመፍታት የወሰዱት ተጨባጭ እርምጃ አለመኖሩ በሌላ በኩል ሌሎች እንዳይታጠቁ እገዳ ለማድረግ መደራደሩ የስምምነቱን አተገባበር ፈታኝ ሲያደርገው ቆይቷል።

ከዚሁ የኒውክለር መሳሪያ ጋር በተገናኘ በዋናነት ከላይ የተመለከቱ መርሆዎችን መነሻ በማድረግ የተመሰረቱ እና የተዘጋጁ ስምምነቶች፣ ፕሮግራሞች፣ ነፃ ቀጣናዎች፣ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች ይገኛሉ። ለአብነት የአለም አቀፍ አቶሚክ ሀይል ኤጀንሲ፣ የኒውክለር አቅራቢ ቡድኖች፣ የኒውክለር ስርጭት ደህንነት ፣ በርካታ የኒውክለር ጦር መሳሪያ ነፃ ቀጣናወች ከብዙ በጥቂቱ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። አገራት ያላቸውን ጠቅላላ ኒውክለር ነክ ቁሳቁሶችን ለአቶሚክ ሀይል ኤጀንሲ እንዲገልጹ

ይጠበቃል። ይህም ኤጀንሲው ኒውክለር የሌላቸው አገራት የኒውክለር ስርጭት እገዳ ስምምነቱን መተግበር አለመተግበራቸውን ለማጣራት እድል ይሰጠዋል። አገሮቹ ፈቅደው ያላቸውን ፋሲሊቲ የማያሳዩ ከሆነ ከላይ የተገለጹ መርሆች ተጥሰው የመገኘት እድል ይከሰታል ። በዘጠናዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በኢራቅ የኪላደሲቲን የኒውክለር የጦር መሳሪያ ፕሮግራም መታየት በአገራት ያልተገለፁ የኒውክለር እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን አመላካች መሆኑን አቶሚክ ኤጀንሲው ይፋ አድርጌ ነበር።

ከላይ የተገለጹ መርሆችን ለማስከበር ከተመሰረቱ ቡድኖች አንዱ የሆነው የኒውክለር አቅራቢ ቡድን የኒውክለር የጦር መሳሪያ ልማትን ከመግታት አንፃር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ቡድኑ በቁጥር ሰላሳ አገራትን ያቀፈ ሲሆን የኒውክለር ግብአት ቁሳቁሶችን፣ ምርቶችን እና ቴክኖሎጂዎችን ለአለም ገበያ የሚያቀርብ ነው። ቡድኑ በኤክስፓርት ላይ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችለው መሪ መመሪያ በማዘጋጀት የጋራ ምክሮችንም ያደርጋል። የኒውክለር አቅራቢ ቡድኑ ዋነኛ አላማ አባላቱ ለገበያ የማያቀርቧቸው ኒውክለር ነክ እቃዎች በተለይም ኒውክለር ለማበልፀግ የሚረዱ ጥሬ እቃዎች እና ቴክኖሎጂዎች የኒውክለር ጦር መሳሪያ ለማምረት ፍላጎቱ ወዳላቸው አገራት እጅ እንዳይገባ ቁጥጥር ማድረግ ነው። የዚህ ቡድን ተግዳሮት ደግሞ አባል አገራቱ የሚዘጋጀውን መሪ መመሪያ የአገራዊ ህጎቻቸው አካል አድርገው እንዲተገብሩት ከማድረግ ባለፈ መመሪያውን የሚያስተገብር ስልጣን ያለው የበላይ አካል የለውም። በመሆኑም አተገባበሩ በአገሮቹ ሙሉ ይሁንታ ላይ የተመሰረተ ነው።

የኒውክለር መሳሪያ ስርጨት ደህንነት ኢንሼቲቪ በበኩሉ ኢ-መደበኛ ኢንቪቲቪ ሲሆን የኒውክለር መሳሪያ ቁሳቁሶች ወደ አሸባሪዎች እንዲሁም መሳሪያውን ለማልማት ፍላጐት እና ፕሮግራም ወዳላቸው አገራት እጅ እንዳይገባ መከላከል ነው።

ይህ ኢንሼቲቪ እ.ኤ.አ. በ2003 በፕረዝደንት ጆርጅ ደቢሊው ቡሽ ይፉ ከሆነ ወዲህ ዘጠና ሰባት አገራት ድጋፋቸውን የገለፁ ሲሆን፣ ሀያ አንድ ማለትም አሜሪካን፣ እንግሊዝ፣ ሩሲያ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ አርጀንቲና እና ጃፓን የመሳሰሉት የኦፕሬሽናል ኤክስፐርት ቡድን አባላት በመሆን ኢንሽቲቩን ያስተግብሩታል። ተሳታፊ አገራት በባህር፣ አየረ እንዲሁም በምድር በሚጓጓዙ የመጓጓዣ አይነቶች ላይ ክትትል በማድረግ አውዳሚ የጦር መሳሪያ እንዲሁም መሳሪውን ለማምረት የሚረዱ የምርት ግብአቶች ወዳልተፈለገ ስፍራ እንዳይጓጓዝ ቁጥጥር ያደርጋሉ።

ይኸኛውም ኢንሼቲቪ የአለምአቀፍ ህግጋት ጉዳዮችን ጥያቄ ውስጥ በማስገባት በአገራት መካከል ቅራኔን የሚያጭሩ ጉዳዮችንም ሲፈጥር የቆየ ነው። የኢንሼቲቩ ተሳታፊ አገራት ማናቸውንም

ተጠራጣሪ መርከቦችን፣ አውሮፕላኖችን እና ደረቅ መሬት ላይ የሚጓጓዙ ተሽከርካሪውን አውዳሚ የጦር መሳሪያ መያዛቸውን ከጠረጠሩ በየትኛውም የውሀ ክልል፣ በማናቸውም ስፍራ በማስቆም ፣ አውሮፕላንም ከሆነ እንዲያርፍ በማስገደድ ማጣራት፣ከተገኘም እርምጃ መውሰድ የኢንሼቲሹ አላማ በመሆኑ እንደተገለጸው ከሉአላዊ አገራትን ድንበር መጣስ ጋር የተያያዙ ውዝግቦችን ሲያስነሳ ቆይቷል፡፡

የኒውክለር ጦር መሳሪያ ነፃ ቀጣና ሌላኛው የስርጭት ቁጥጥር መንገድ ነው፡፡ በእነዚህ ቀጣናዎች መሰሪያውን ማልማት፣ ማምረት፣ ማከማቸት፣ በግዥም ሆነ በተለያየ መንገድ ባለቤት መሆን ህገ-ወጥ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የተለያዩ ቀጠናዎች በተለያዩ አህጉራት ይገኛሉ፡፡ ለአብነት የአንታርቲክ ስምምነት ፣ሳውዝ- ፖስፊክ-የራሮቶንጋ ስምምነት፣ የላቲን አሜሪካ እና ካሪቢያን- የትላቴሎኮ ስምምነት፣ የደቡባዊ ምስራቅ ኤዥያ- ባንኩክ ስምምነት፣ አፍሪካ- ፔሊንዳባ ስምምነት የነፃ ቀጣናዎቹ ምስረታ ስምምነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ስምምነቶች ነጻ ቀጠና ከመመስርት ጎን የኒውክለርን መስፋፋት እና የኒውክለር መሳሪያ ባለቤቶች ያላቸውን ክምችት እንዲቀንሱ የሚጠይቁም ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁሉም መንገዶች አውዳሚ የጦር መሳሪያውን መስፋፋት ለመግታት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው፡፡ ሆኖም አለምአቀፍ ስልጣን ተሰጥቶት በበላይነት የሚያስፈጽም አካል እስከሌለ ድረስ አገራት ወይም መንግስታት ችላ ካሉት የሚፈለጉ ውጤቶችን ማስመዝገብ አይቻልም፡፡ አብዛኞቹ የሚተገበሩት በአገራት በጎ ፍቃድ ላይ በመመስረት በመሆኑ፡፡ ለዚህም ነው ህንድ፣ ፖኪስታን፣ እስራኤል እና ሰሜን ኮሪያ ወደ ባለቤትነት እንደ ተሸጋገሩ የሚነገረው ፡፡ ሰሜን ኮሪያ የኒውክለር ስርጭት እገዳ ስምምነት ፈራሚ አገር ብትሆንም ግዴታዋን ምን ያህል ወደ ጐን እንዳለች ሰሞነኛውን የአለም የፓለቲካ ትኩሳት መመልከት በቂ ነው፡፡ በአሜሪካ አንዷት ግዛት ላይ ጥቃት ለመሰንዘርም ዝግጅቷን ማጠናቀቋን ይፋ አድርጋለች፡፡ አሜሪካም በበኩሏ አንዷት ጥቃት ከተፈጸመብኝ አጸፋዊ እርምጃ ለመውሰድ ሁሉን ሸክፊያለው ብላለች፡፡ ከጃፓን ጋም የወታደራዊ ልምምድ ጀምራለች፡፡ ሰሜን ኮሪያ ተደደጋሚ ሚሳኤል የማስወንጨም ሙከራ ስታካሂድ መቆየቷ ለዚህ የአለም አቀፉ ማህበረሰብ ተደጋሚ ማስጠንቀቂያ እየሰጠ እና ማዕቀብ እየጣለ ቢቆይም አገሪቱ ከድርጊቷ ልትታቀብ አለመቻሏ አሁን ለተከሰተው አለምአቀፍ የኒውክለር ውጥረት አለምን አስገብቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከኒውክለር የጦር መሳሪያ ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ካለፉት የቀዝቃዛው ጦርነት ልምዶች የተለየ አመለካከት ይንፀባረቃሉ፡፡ አንደኛው አመለካከት የኒውክለር ባለቤት የሆኑ አገራት መበራከት

ለአለም ሰላም አወንታዊ ሚና አለው የሚለው ነው። መሳሪያውን የታጠቁ አገራት መበራከት መሳሪያው ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደርጋል የሚል መነሻ አለው ። ለዚህም መከራከሪያው መሳሪያው በአንደኛው ወገን ጥቅም ላይ የሚውልበት አጋጣሚ የሚከሰት ከሆነ ሌላኛው የታጠቀ በመሆኑ የመጠቀሙ እድል ይሰፋል ። በዚህም አሸናፊ እና ተሸናፊ በሌለበት የጋራ ጥፋት እና ውድመት ይመጣል ። በመሆኑም  በአገራት መካከል የሀይል ሚዛንን ብቻ በመጠበቅ ከመፈራራት የመነጨ መከባበር ስለሚፈጥር መሳሪያውን የሚታጠቁ አገራት መብዛት በአለም ሰላም ያሰፍናል የሚል አስተሳሰብ የሚያራምዱ ናቸው።  ሌላኛው አስተሳሰብ ደግሞ የኒውክለር መሳሪያ ታጣቂ አገራት ቁጥር መጨመር ከተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች አንፃር ለእልቂት በር የሚከፍት እንደሆነ የሚያምን ነው።

የኒውክለር ባለቤት አገራት ቁጥር መጨመር ለእልቂት በር የሚከፍቱ ስለመሆናቸው የሚነሱ ነባራዊ ምክንያቶችን እንመልከት፡-

- የኒውክለር ባለቤት ለመሆን የሚተልሙ እና እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የተወሰኑ አገራት መሪዎች የግል ባህሪ ጨካኝ መሆን ። እነኝህ መሪዎች መሳሪያውን ካለሙት በኃላ በማንኛውም ባሻቸው ጊዜ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ። ከዚህ አንጻር የሰሜን ኮሪያው ኪም ጆንግ እንዲሁም የአሁኑ የአገሪቱ መሪ ከአለም መሪዎች ተገልሎ መኖራቸው፣ የአገሩ ህዝብ በድህነት ሲማቅቅ አገሪቱን ካላት የኢኮኖሚ አቅም በላይ በጦር ሀይል በማጠናከር ከአለም ቁንጮ አድርገዋታል። የሚያስተዳድረው ሕዝብ በረሀብ እየተገረፈ አገሪቱን የመሳሪያ ክምችት አድርጎታል።  ከዚህ የበለጠ ጭካኔ የለም ። በመሆኑም ሰውየው በሌሎች ጠላቶቼ በሚላቸው አገራት ላይ የኒውክለር ቦምብ ለመጣል ወደ ኋላ  የማይል ነበር፣የአሁኑም እንደዛው  ። በወግ አጥባቂው በሺያ ሙላህ የምትመራዋ ኢራን እ.ኤ.አ በ2005 ፕሬዝዳንት ማህመድ አህመድ ነጃድ የአገሪቱ መሪ አድርጋ በመረጠቻቸው ወቅት በአንደበታቸው ስለ እስራኤል ሲናገሩ፣፣ ‹‹ ከአለም ካርታ መጥፋት ያለባት አገር›› ብለዋል። እንደዚህ አይነት ጭካኔ የተሞላበት የጥላቻ አስተሳሰብ ያላቸው መሪዎች ለጥፋት ወደሓላ አይሉም ።

በመሆኑም ሰዎቹ በዚህ ባህሪያቸው እና ፍላጐታቸው ጉዳዬን እጃቸው ላይ ካስገቡ አደጋው የከፋ ሊሆን እንደሚችል ይነገራል።

- በርከት ያሉ አገራት የኒውክለር የጦር መሳሪያ ባለበት ከሆኑ የሰውም ሆነ ቴክኒካል ስህተቶች አደጋዎችን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ፣

- በአሁን ወቅት የኒውክለር የጦር መሳሪያ ባለቤት ለመሆን የሚፈልጉ አገራት እንዲሁም ባለቤቶቹ በተለያዩ ጉዳዮች ምክንያት አለመግባባት የሰፈነባቸው የጦርነት አየር የሚነፍስባቸው ቀጣናዎች መሆናቸው። ለአብነት ፓኪስታን እና ህንድ በካሽሚር ጉዳይ፣ ኢራን እና እስራኤል በጠላትነት የሚታዩ መሆናቸው፣ የኮሪያ ባህረሰላጤ በአለም አደገኛ ከሚባሉ ስፍራዎች አንዱ መሆኑ።
- የአውዳሚ መሰሪያውን የሚታጠቁ አዳዲስ አገራት መፈጠር ሌሎችም እንዲታጠቁ ማነሳሻ መሆኑ ይህም አደጋውን ከፍ እንደሚያደርግ፣ በኢሲያ አህጉር የሰሜን ኮሪያ ኒውክለር የመታጠቅ ምልክት ፣ ጃፓን ማበልፀጓን እንድትቀጥል በር መክፈቱ(ለጊዜው ለሀይል ጥቅም ቢሆንም) ፣ በሺያ አስተዳደር ስር ያለው ኢራን ከታጠቀ የሱኒ አረብ አገራትን እንደ ሳዑዲ አረቢያ ያሉትን እንደሚያነሳሳ በአብነት ይነሳል።
- አዳዲሶቹ የኒውክለር ታጣቂ አገራት የመሰሪያው አያያዝ ልምድ ስለማይኖራቸው ከዚሁ ጋር የተገናኘ ችግሮች ቢከሰቱ በበቂ ሁኔታ የመከላከል አቅም ማደራጀት ስለማይችሉ የጠላት ጥቃት ከተከሰተባቸው ውድመቱ የከፋ መዘዙም ከባድ ይሆናል።
- የኒውክለር የጦር መሳሪያ መበራከት በአሸባሪዎች እጅ መሳሪያው እንዲገባ ከፍተኛ ዕድል ይፈጥራል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ ጉዳዮች የኒውክለር መሳሪያ መስፋፋትን ከሰላሙ ይልቅ ጥፋቱ ይበዛል የሚሉ ጠበብቶች የሚያስቀምጧቸው ምክኒያቶች ናቸው።

የኒውክለርን አውዳሚነት እና ዘመን ተሸጋሪ መዘዝ ጃፓናውያን በተግባር አይተውታል ፣የተቀረው አለምም ሰምቶታል ። ሆኖም ዛሬም ድረስ የኒውክለር ጉዳይ አገራትን ወደ ፓለቲካ እና ወታደራዊ ውጥረት ከቷል። አገራት ኒውክለርን ለሰላማዊ እና ሀይል ምንጭነት እንዲጠቀሙ በሩ ክፍት መሆኑ ፣ይሄን ለማስፈተሽ እና ለማሳየት ፍቃደኛ ለመሆን የሚያሳዩት ዳተኛነት ሌላው የአለማችን ችግር እየሆነ መጥቷል። የሀይል ሚዛን ጥበቃ የሚባል አስተሳሰብ አገራትን አላስፈላጊ ፉክክር ውስጥ እንዲገቡ ከማድረግ ባሻገር የባላንጣነትን መንፈስ እያፋፋ፣ በአንጻሩ ወደ ፍጥጫ እንዲገቡ የሚጋብዝ ሆኖአል ። የኒውክለር ታጣቂ አገራት የአለም ዘብ እና ተቆጣጣሪ መንግስት ለመሆን የሚያሳዩት አዝማሚያ በሌሎች ላይ የሚፈጥረው የደህንነት ስጋት ፣በኒውክለር መሳሪያ ፍተሻ ሰበብ የሚፈጸሙ የሉአላዊነት ጥሰቶች እና በደሎች ፣እነኝህ ሁሉ የኒውክለር ጥያቄዎች በአንድ ትውልድ ብቻ የማይመለሱ ቢሆንም በየደረጃው የሚያስፈልገው ምላሽ ካልተሰጠ ኒውክለር ለአለም ህዝብ ስጋት እንጅ ሰላም እና እድገት ሊያመጣ አይችልም ።

አገራችን ኢትዮጵያ ኒውክለርን ለሰላማዊ አላማ ለመጠቀም ፍላጎት ካላቸው አገራት አንዷ ነች ። እ.ኤ.አ በ2037 የኤሌክትሪክ ሀይል መጠኑዋ ወደ 37,000ሜጋ ዋት ለማድረስ ፍላጎት ያላት ሲሆን ከዚሁ መጠን 1200ሜጋ ዋት ከኒውክለር ሀይል የሚመነጭ እንደሆነ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን ለእርዳታ ሰጭዎች፣ፋይናንሰሮች እና ሙሁራን በተዘጋጀ መድረክ ላይ ከወራቶች በፊት አሳውቆአል ።

ከዚህም በተጨማሪ በቅርቡ እ.ኤ.አ ጁን ቀን 2017 የኢትዮጵያ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከሩሲያ አንድ ተቋም ጋር የኒውክለር መሰረተ ልማት ማልማት የሚያስችል ስምምነት ተፈራርሞአል። በስምምነቱ መሰረት የኒውክለር ቴክኖሎጀን አስመልክቶ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የሚፈጥሩ ፕሮግራሞችን ለመተግበር እንዲሁም በግብርና እና ህክምና ዘርፍ የኒውክለር ውጤቶችን መጠቀም የሚቻልባቸውን እድሎች መፍጠርን ታሳቢ ያደረገ ነው።

ይህ ስምምነት ኒውክለርን ለሰላማዊ ጥቅም ለማዋል አገራች ከሌላ አገር ጋር የፈረመችው የመጀመሪያው ስምምነት ነው። በመሆኑም አገራችንም በሂደት ለሰላማዊ ጥቅም የሚውል ኒውክለር ባለቤት የምትሆን ከሆነ የተለያዩ አለም አቀፍ ግዴታዎች ውስጥ መግባትዋ የማይቀር ይሆናል ። አንደኛው በአቶሚክ ኤጄንሲ በየጊዜው ለመፈተሽ በሩዋን ክፍት ማድረግ ይሆናል።

ሰላም